ብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ጳውሎስ

በዲ/ን ቴዎድሮስ ኃይሉ

- በትግራይ ክልል በአድዋ በእንዳባ ገሪማ ገዳም አጥቢያ ከአባታቸው ከአፈ መምህር ገብረ ዮሐንስ ወልደ ሥላሴና ከእናታቸው ከወ/ሮ አራደች ተድላ ጥቅምት 25 ቀን 1928 ዓ.ም ተወለዱ፡፡
- በአባ ገሪማ ገዳም ከስድስት ዓመት ዕድሜአቸው ጀምረው ሥርዐተ ገዳማትንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት እያጠኑ ካደጉ በኋላ ዲቁና ከአቡነ ማርቆስ  ቀጥሎም የቅስና ማዕረግ ከአቡነ ይስሐቅ ተቀበሉ፡፡
- ባደጉበትና ትሩፋትን በፈጸሙበት በአባ ገሪማ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ተቀበሉ፡፡
- በ1949 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በወቅቱ የቅድሥት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የበላይ ኃላፊ በነበሩት በአቡነ ቴዎፍሎስ ፈቃድ በኮሌጁ በአዳሪ ተማሪነት ዘመናዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት በመከታተል የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀቁ፡፡
- በትምህርት ገበታቸው ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ከንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ 3 ጊዜ ሽልማት ተቀብለዋል፡፡
- ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መስከረም 1975 ዓ.ም የጵጵስና ማዕረግ ተቀበሉ፡፡
- በሜይ 1962 በቅዱስ ቭላድሚር የሩሲያ ኦርቶዶክስ ሲሜናርየም በዲፕሎማ፣ በሜይ 1966 በበርክሌይ ዲቪኒቲ ት/ቤት በባችለር ዲግሪ፣ በሜይ 1972 በፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ዲቪኒቲ በማስተርስ፣ በሜይ 1988 በፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ዲቪኒቲ በዶክትሬት  ተመረቁ፡፡
- ሰኔ 28 ቀን 1984 ዓ.ም አምስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በመሆን ተመረጡ፡፡
- በዘጠነኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው በ1998 ዓ.ም ተሾሙ፡፡
- ከዚህ ዓለም ረቡዕ ለሐሙስ አጥቢያ ነሐሴ 10 ቀን 2004 ዓ.ም በሞተ ሥጋ ተለዩ፡፡

## <u>አገልግሎት</u>

በሀገር ውስጥ

ለ15 ዓመታት በዲቁናና በምንኩስና በአባ ገሪማ ገዳም አገልግለዋል፡፡

- ለ8 ዓመታት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በመደበኛ ቀዳሽነት አገልግለዋል፡፡
- በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲን በመሆን ትምህርት ቤቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ጥረዋል፡፡
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ፣ የድርሰት፣ የስብከተ ወንጌል፣ የጋዜጦች፣ የመጽሔቶችና የሬዲዮ መመሪያ በመሆን ሰፊ የሆነ ሐዋርያዊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡
- ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናዊ መልክ ለተቋቋመው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማዕከላዊ ቢሮ መሥራች አባት በመሆን ፈር ቀደዋል፡፡

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የስደተኞች አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሐፊና የልማት ኮሚሽን ዋና ዳይሬክተር በመሆን ከ1974 እስከ 1976 እ.ኤ.አ ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል፡፡

- በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በዳይሬክተርነት ሰርተዋል፡፡

- ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ተወርሶ የቆየው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጥቅምት 12 ቀን 1987 ዓ.ም እንዲከፈት አድርገዋል፡፡

- የቤተ ክርስቲያን መሬት፣ ንብረት፣ ሕንፃዎች እንዲመለሱ አደርገዋል፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ባርከው ከፍተዋል፡፡ የተለያዩ ዓለም ዐቀፍ ስብሰባዎችን በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደርገዋል፡፡ የሰላምና የዕርቅ ጉባኤዎችን አስተባብረዋል፡፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን አገለግለዋል፡፡

*__በውጭ ሀገር__*

እ.ኤ.አ ከ1967 ጀምሮ የኢትዮጳያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወኪል በመሆን፡-

- ❖ በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ቋሚ ኮሚቴ፤
- ❖ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በባይብል ሶሳይቲ፤
- ❖ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር እርሸና እንደስትርያል ሚሽን የከተማ አካባቢ ሐዋርያ፤
- ❖ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር እምነትና ሥርዓት ኮሚሽን ለሰባት ዓመት፤
- ❖ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የማእከላዊ ኮሚቴ ለሰባት ዓመት በአባልነት፤ አገልግለዋል፡፡

እ.ኤ.አ በ1667 ዓ.ም በሞንትሪያል የዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን የኢትዮጵያን ልዑካንን ለ8 ወራት መርተዋል፡፡

በ1992 እ.ኤ.አ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ለ7 ዓመታት በአማካሪነት ተሠይመው በኦቪያን ፈረንሳይ በተካሄደው ስብሰባ ተሳትፈዋል፡፡

ከ1984 እ.አ.ኤ ጀምሮ በስደት ላሉ ምዕመናን የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን በኒዮርክ፣ የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን በዳላስ ቴክሳስ፣ የደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን በሎስአንጀለስ ካሊፎረኒያ፣ የደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በሳንዲያጎ ካሊፎርኒያ፤ የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በታምፓ ፍሎሪዳ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በላስቬጋስ ናሸዳ እንዲሁም ስድስት መንፈሳዊ ማኅበራት (የመድኃኔዓለም፣ የቅድስት ድንግል ማርያም፣ የኪዳነ ምሕረት፣ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ገብርኤልን) አቋቁመዋል፡፡

*__ቋንቋ__*

ከትግርኛና ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ዕብራይስጥና ግሪክ ቋንቋን ለመመርምርና ለንባብ በቂ የሆነ ችሎታ አላቸው፡፡

ቅዱስነታቸው 5ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው መመረጣቸው በተነገረበት ወቅት በሰጡት አባታዊ ምላሽ «የእኛ የካህናት ተልዕኮ የእግዚአብሔር ጥሪ እንጂ እንደሌላው ተርታ ሥራ አይደለም፤ እግዚአብሔር ሲጠራ እንቢ ማለት የሚችልም የለም፡፡ የተመረጥኩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዳለፈው ጊዜ በሞግዚት በምትሠራበት ወቅት ቢሆን ኖሮ ምረጫውን አልቀበለውም ነበር፤ ነገር ግን የመረጣችሁኝ የአባቶች መሥዋዕትነት ይበልጥ በሚጠበቅበት በዚህ ፈታኝ የሽግግር ወቅት በመሆኑ ምርጫውን በደስታ ተቀብዬዋለሁ፤ የተቀበልኩትም በሹመት መከል ልከብርበት ወይም ልመካበትና አባ፤ አባ ልባልበት አይደለም የተጠየቀውን የአባትነት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ባስቻለኝ መጠን ልከፍልበት እንጂ» ብለው ተናገሩ፡፡